የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አስራ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፫
አዲስ አበባ ሚያዝያ ፫ ቀን ፲፱፻፺፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

13th Year No. 23
ADDIS ABABA – 11th April 2007

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፩፻፴፫/፲፱፻፺፱ ዓ.ም.
ወደአገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ስለተጣለ ተጨማሪ ቀረጥ
የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ
ገጽ ................................................................ ፫ሺ፭፻፺፯

*CONTENTS*

Regulations No. 133/2007
Import Sur-Tax Council of Ministers Regulations
Page ........................................................ 3597

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፴፫/፲፱፻፺፱

### ወደ አገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ተጨማሪ ቀረጥ ለማስከፈል የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፯ አንቀጽ ፭ እና በተዋሀደ የሸቀጦች አሰያየምና አመዳደብ ሥርዓት ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፷፯/፲፱፻፹፮ አንቀጽ ፬ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "ወደአገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ስለተጣለ ተጨማሪ ቀረጥ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፴፫/፲፱፻፺፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. የተፈፃሚነት ወሰን

በዚህ ደንብ የተጣለው ተጨማሪ ቀረጥ ተፈፃሚ የሚሆነው በደንቡ አንቀጽ ፭ ነፃ ከተደረጉት በስተቀር በማናቸውም ወደኢትዮጵያ በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ይሆናል፡፡

፫. የተጨማሪ ቀረጥ ማስከፈያ ልክ

በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ወደአገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ፲ ፐርሰንት (አሥር በመቶ) ተጨማሪ ቀረጥ እየተጣለ ይሰበሰባል፡፡

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS No..133 /2007

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO PROVIDE FOR THE PAYMENT OF SUR-TAX ON IMPORT OF GOODS

These Regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 471/2005 and Article 4 of the International Convention on the Harmonized Commodity Description and Coding system Ratification Proclamation No. 67/1993.

1. *Short Title*

These Regulations may be cited as the "Import Sur-Tax Council of Ministers Regulations No.133/2007"

2. *Scope of Application*

The Sur-tax levied under these Regulations shall apply to all goods imported into Ethiopia except those exempted under Article 5 of these Regulations.

3. *Rate of the Sur-tax*

Without prejudice to Article 5 of these Regulations Sur-tax of 10% shall be levied and collected on goods imported.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ ፩
Negarit G. P.O. Box 80,001

፬. <u>የስሌቱ መሠረት</u>

በዚህ ደንብ መሠረት ለሚከፈለው ተጨማሪ ቀረጥ የስሌቱ መሠረት:-

፩. የዕቃው ዋጋ፣ የመድን አረቦን እና የማስጫኛ ወጪ (ሲ.አይ.ኤፍ)

፪. በዕቃው ላይ ሊከፈል የሚገባው የጉምሩክ ቀረጥ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የኤክሣይዝ ታክስ፣

ድምር ይሆናል::

፭. <u>ከተጨማሪው ቀረጥ ነፃ ስለመሆን</u>

፩. ከዚህ በታች የተመለከቱት ከተጨማሪው ቀረጥ ነፃ ናቸው::

ሀ) ከዚህ ደንብ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ሠንጠረዥ የተዘረዘሩ ዕቃዎች፣

ለ) በሕግ፣ በመመሪያ ወይም መንግሥት ባደረገው ስምምነት ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ የተደረጉ ሰዎች እና ድርጅቶች የሚያስመጧቸው ዕቃዎች፣

፪. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በዚህ ደንብ ከተጨማሪ ቀረጥ ነፃ ሆነው ወደአገር እንዲገቡ የተፈቀደውን ዕቃዎች ዝርዝር ሊጨምር ወይም ሊቀንስ እንዲሁም ለዚህ ደንብ አፈፃፀም የሚያግዙ መመሪያዎችን ሊያወጣ የችላል::

፮. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከሚያዝያ ፫ ቀን ፲፱፻፺፱ ጀምሮ የፀና ይሆናል::

አዲስ አበባ ግንቦት ፱ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ

ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

ሠንጠረዥ

<u>ተጨማሪ ቀረጥ (ሱር ታክስ) የማይመለከታቸው ዕቃዎች ዝርዝር</u>

፩. የመሬት ማዳበሪያዎች፣

፪. ነዳጅ፣ የብረታ ብረት ቅባቶች፣

፫. የጭነትና የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች እና ለተለየ አገልግሎት የሚውሉ ተሽከርካሪዎች፣

፬. አውሮፕላኖች፣ የአየር መንኩራኩሮች፣ የጠፈር መንኩራኩሮች እና የነዚሁ ክፍሎች፣

፭. የካፒታል (የኢንቨስትመንት) ዕቃዎች፣

4. *Basis of Computation*

The basis of computation for the sur-tax levied under these Regulations shall be the Aggregate of:

1. Cost, insurance, Freight (CIF) value;
2. Customs duty, value Added Tax and Excise Tax Payable on the good.

5. *Exemption from the Sur-Tax*

1. The following shall be exempted from the Sur-tax:
   a) goods listed in the Schedule attached to these Regulations;
   b) goods imported by persons or organizations exempted from customs duty by law, directives or by agreement entered into by the Government.
2. The Minister of Finance and Economic Development may at his own discretion increase or decrease the items exempted from the Sur-tax under these Regulations and issue directives for the proper implementation of these Regulations.

6. *Effective Date*

These Regulations shall enter into force as of 11 th day of April 2007.

Done at Addis Ababa, this 17 th day of May 2007

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

SCHEDULE

*ITEMS EXEMPTED FROM SUR-TAX*

1. Fertilizers;
2. Petroleum and lubricants;
3. Motor Vehicles for freight and passengers, and special purpose motor vehicles;
4. Aircraft, spacecraft, and parts thereof;
5. Capital (Investment goods).